አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

## OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፪
አዲስ አበባ ፪ሺህ፪ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2[nd] year No 22
ADDIS ABABA 2010

ማውጫ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ

**CONTENTS**

**The Addis Ababa city Government Immovable Property Registration and Information Agency Establishment Proclamation**

### አዋጅ ቁጥር ፳፪/፪ሺህ፪
### በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ

በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት፣ ባለይዞታነት እና በንብረቱ ላይ የሚከናወኑ የተለያዩ ህጋዊ ተግባራት የመመዝገብ ሂደቱን ቀልጣፋና ግልጽ ለማድረግ የተቋሙ መቋቋም አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

ዋስትና ያለውና አስተማማኝ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የከተማ ቦታ ነክ ንብረትን ለብድር መያዣነት መስጠትን በማበረታት የከተማዋን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ማፋጠን በማስፈለጉ፣

የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ የሚያካሄደውን ተቋም ሥልጣንና ተግባር በህግ መወሰን አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

### Proclamation No. 22 /2010
### The Addis Ababa city Government Immovable Property Registration and Information Agency Establishment Proclamation

**Whereas**, it is believed necessary to establish an institution to make expedient and transparent the process of registering the right of ownership, possession and other legal acts undertaken on immovable property situated in Addis Ababa City;

**Whereas**, it is found necessary to fasten the economic and social development of the City by introducing secured and reliable work procedure and encouraging mortgage of land-related property as security for loan;

**Whereas**, it is believed to be necessary to define by law powers and functions of the institution undertaking registration of immovable property;

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፳፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.85

በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፲፬/፩/ሀ/ መሠረት የሚከተለዉ ታዉጇል።

Now therefore, in accordance with Article 14(1)(a) of the Revised Charter Proclamation No. 361/2003 of the Addis Ababa City Government it is proclaimed as follows;

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር "የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፳፪/፪ሺህ፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪ ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሠጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

፩ «ከተማ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፣

፪ «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፣

፫ «ከንቲባ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ነዉ፣

፬ «የማይንቀሳቀስ ንብረት» ማለት መሬት እና ቤት ነው፣

፭ «መሬት» ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማስተር ፕላን ክልል ዉስጥ ያለ ሆኖ ለተቋም ወይም ግለሰብ መሬቱን እንዲጠቀምበት ሥልጣን ባለዉ አካል የተፈቀደ ይዞታ ማለት ነዉ፤

፮ «ቤት» ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ክልል ዉስጥ ባለ መሬት ላይ የከተማዉ የመሬት አጠቃቀም ፕላን በሚፈቅደዉ መሠረትና የቤቱ የግንባታ ፈቃድ ቤት እንዲገነባ ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን ባለዉ አካል ስምምነት ተሰጥቶ ለቋሚና ዘላቂ አገልግሎት የተገነባ የመንግሥት፣ የግል መኖሪያ፣ የንግድ፣ የእምነት፣ መንግሥታዊ ላልሆነ ተቋም፣ ወይም ለማህበራዊ አገልግሎት የሚዉል ቤት ወይም ህንጻ ማለት ነው፤

፯ «ኤጀንሲ» ማለት በዚህ አዋጅ የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ነው፣

፰ «ጽህፈት ቤት» ማለት በክፍለ ከተማ ደረጃ የሚቋቋም የኤጀንሲውን ተግባራት የሚፈጽም የሥራ ዕርከን ነው፣

## Part One
## General

1. **Short Title**

This proclamation may be cited as the "Addis Ababa City Government Immovable Property Registration and Information Agency Establishment Proclamation No 22 /2010."

2. **Definition**

Unless the context demands otherwise, in this proclamation;-

1. " City " means the Addis Ababa City;
2. "Government" means the Addis Ababa City Government;
3. “Mayor” means Mayor of the Addis Ababa City;
4. " Immovable property " means land and house;
5. “Land” means a plot of land situated within the master plan of Addis Ababa City and a possession permitted for institutional or individual use by authorized organ;
6. “House” means a house or building built on a plot of land situated within the boundary of Addis Ababa City in accordance with the land use plan of the City and fixed and permanently built in accordance with the construction permit issued by a body so authorized and serving for government institution, private residence, business, religious, non-governmental organization, or social services;
7. "Agency" means the Addis Ababa City Government Immovable Property Registration and Information Agency established in accordance with this proclamation;
8. "Office" means a structure established to discharge functions of the Agency at Sub-city level ;

፱ «ዳይሬክተር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ዳይሬክተር ነው፣

፲ «ምክትል የምዝገባና መረጃ ዳይሬክተር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ምክትል የምዝገባና መረጃ ዳይሬክተር ነው፣

፲፩ «ምክትል የቅየሳ ዳይሬክተር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ምክትል የቅየሳ ዳይሬክተር ነው፣

፲፪ «ሰው» ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት ያለው አካል ነው፣

፲፫ «መረጃ» ማለት የማይንቀሳቀስ ንብረት የይዞታ፣ የባለቤትነት እና ሌሎች ተዛማጅ ህጋዊ ተግባራት መረጃ ነው::

፲፬ «ሥራ አስኪያጅ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራ አስኪያጅ ነው::

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በአዲስ አበባ ከተማ ክልል በሚገኝ ማንኛ ውም የማይንቀሳቀስ ንብረት በሚመለከት ተፈፃሚነት ይኖረዋል::

## ፬. መቋቋም

፩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና የመረጃ ኤጀንሲ (ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲ" ተብሎ የሚጠራው) ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣

፪ ኤጀንሲዉ የሚመራዉ በቦርድ ይሆናል፤ ዝርዝሩ በካቢኔ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፣

፫ የኤጀንሲው ቦርድ ተጠሪነቱ ለከተማው ስራ አስኪያጅ ይሆናል፣

## ፭. ዋና መሥሪያ ቤት

፩ የኤጀንሲው ዋና መሥሪያ ቤት በማዕከል በከተማ ደረጃ ይሆናል፣

፪ ኤጀንሲው በክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል::

## ፮. የኤጀንሲው አደረጃጀት

ኤጀንሲዉ፡-

፩ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባና መረጃ ዋና ዳይሬክተር፣

፪ አንድ የምዝገባና መረጃ ምክትል ዳይሬክተር እና አንድ የቅየሳ ምክትል ዳይሬክተር፣



9. "Director" means the Addis Ababa City Government Immovable Property Registration and Information Agency director;
10. "Deputy registration and information director" means the Addis Ababa City Government Immovable Property Registration and Information Agency deputy registration and information director;
11. "Deputy survey director" means the Addis Ababa City Government Immovable Property Registration and Information Agency deputy survey director;
12. "Person " means any physical person or an entity entrusted with personality by law;
13. "Information" means the information of possession, ownership and other related legal acts of immovable property;
14. "Manager" means the Addis Ababa City Manager.

## 3. Scope of Application

This proclamation shall be applicable on any immovable property situated within the boundary of Addis Ababa City.

## 4. Establishment

1. The Addis Ababa City Government Immovable Property Registration and Information Agency (hereafter called "the agency") is hereby established having its own legal personality.
2. The Agency shall be directed by a Board; details shall be determined by a regulation issued by the Cabinet of the City.
3. Board of the Agency shall be accountable to the City Manager.

## 5. Head Office

1. The Agency shall have its head office at City level.
2. The Agency shall have office at Sub-city level.

## 6. Organization of the Agency

The Agency shall have:-

1. Immovable property registration and information director;
2. one registration and information deputy director and one survey deputy director; and

፫ ተግባርና ሀላፊነቱን ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፣

**፯. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት፦**

ኤጀንሲው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት ይመዘግባል፣ ጠቅላላ መዝገብ ይይዛል፣ መረጃን ያደራጃል፣ በተጠየቀ ጊዜ ለተገልጋዮች መረጃ ይሰጣል፣

፪ የማይንቀሳቀስ ንብረት መዛግብት ለህዝብ ክፍት እንዲሆኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

፫ በማዕከልም ሆነ በጽህፈት ቤት ለሚከናወኑት ተግባራትና ለሚሰጡት አገልግሎቶች ግልጽነትና ቅልጥፍና የሚያግዙ የአሠራር ማንዋሎችን ያዘጋጃል፤ በሰነዶች ላይ የስልጠና ፕሮግራም ያዘጋጃል፣ የስራ ላይ ስልጠና ይሰጣል፣

፬ ተግባራቱን በሚመለከት በፌዴራል ደረጃ የሚወጡ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች ተግባራዊ ያደርጋል፤ በጽህፈት ቤቶችም ተግባራዊ መደረጋቸውን ያረጋግጣል፤

፭ መሻሻል ያለባቸውንም ህጎችና አሠራሮች እንዲሻሻሉ የማሻሻያ ኃሳብ አዘጋጅቶ ለሚመለከተው የበላይ አካል ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣

፮ የማይንቀሳቀስ ንብረት መረጃ ይተነትናል፣ ጥቅም ላይ ያውላል፣

፯ በአስተዳደሩ የበላይ አመራር የሚፈለጉ የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ መረጃዎችን በወቅቱ በተገቢው ፎርማት ይልካል፣

፰ በህግ መሠረት የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤

፱ በስሙ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል።

**፰. የጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባራት**

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩ የማይንቀሳቀስ ንብረት መለያ ኮድ ይሰጣል፤

፪ የማይንቀሳቀስ ንብረት ይዞታ ወይም ባለቤትነት ይመዘግባል፣

፫ የማይንቀሳቀስ ንብረት መረጃዎችን ያደራጃል፣ ይጠቀማል፣ ለሌሎችም ያስተላልፋል፣ የምዝገባ ማረጋገጫ ይሰጣል፤

፬ በጽሕፈት ቤቱ የሚገኝ የማይንቀሳቀስ ንብረት መረጃ ያድሳል፣ ለአገልግሎቱ ቀልጣፋነትና ዉጤታማነት አመቺ የሆኑ አዳዲስ አሠራሮችን ይቀይሳል፣ የተደረገውን ለውጥ ለኤጀንሲው ያሳውቃል፤

3. Other staff necessary to discharge its functions and responsibilities.

**7. Power and Functions of the Agency**

The Agency shall have the following power and functions:-

1. Register, keep principal archive, organize, and provide information, up on request, as regards immovable property situated in Addis Ababa City;
2. Facilitate conditions in which register of immovable property shall be made open to the public;
3. Prepare working manuals assisting the expedience and transparency of the functions and service rendered at City as well as office level; prepare training program on documents and offer on the job training;
4. Implement relevant laws of the Federal Government concerning its functions; ensure that same is implemented in offices at Sub-city level;
5. Propose amendment of laws and procedures that need to be amended and submit to the concerned superior organ; implement same up on approval;
6. Analyze and use information of immovable property;
7. Send, timely and in appropriate format, information of immovable property registration requested by superior officials of the City Government;
8. Collect fee in accordance with law;
9. Own property, conclude contract, sue and be sued, in its name.

**8. Power and Functions of the Office**

The office about shall have the following power and functions:-

1. Issue identification code of immovable property;
2. Register ownership or possession of immovable property;
3. Organize information of immovable property, use, transfer same to others; issue certificate of registration;
4. Renew data of immovable property found in the office; design new working procedures that enable expediency and effectiveness of its service and notify the Agency the change made;

፭ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ወይም ይዞታ ሥም ዝውውር ይመዘግባል፤

፮ የመሬት ይዞታ አቀማመጥና ሌሎች የምዝገባው ቅጅዎችን ህጋዊ ለሆነ ሰዉ ይሰጣል፤

፯ የቅየሳ መረጃ ሲቀርብ የተከፋፈለ ወይም የተቀላቀለ የመሬት ይዞታን ይመዘግባል፣ ስለመመዝገቡም ማረጋገጫ ይሠጣል፤

፰ ከባንክም ሆነ ከሌሎች ህጋዊ ተቋማት የሚቀርብ የዋስትና፣ የፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ፣ የተሰረዙ ካርታዎች ይመዘግባል፤

፱ የአስተዳደሩን የማይንቀሳቀስ ንብረት ይመዘግባል፣ ማስረጃዎች ይሰጣል፤

፲ በማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ ላይ የጎደለ ወይም ያልተስተካከለ መረጃ ሲኖር አግባብነት ባለው የፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ መሠረት ያቃናል፤

፲፩ ከኤጀንሲው የሚሰጡ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን ያከናውናል::

## ክፍል ሁለት

## ስለ ኤጀንሲዉ ዳይሬክተር እና ምክትል ዳይሬክተሮች አሿሿም፣ ስልጣንና ተግባር

### ፱. ስለኤጀንሲው ዳይሬክተር

፩ የኤጀንሲው ዳሬክተር በከተማዉ ስራ አስኪያጅ አቅራቢነት በከንቲባው ይሾማል::

፪ የዳይሬክተሩ የስራ ዘመን ሦስት አመት ይሆናል::

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው ቢኖርም ዳይሬክተሩ ለሁለተኛ ጊዜ ሊሾም ይችላል::

### ፲. የዳይሬክተሩ ስልጣንና ተግባር

ዳይሬክተሩ:-

፩ ኤጀንሲውን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ የኤጀንሲዉን ሥልጣንና ተግባራት ያስፈጽማል::

፪ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባራት ያከናውናል:-



5. Register the transfer of ownership or possession title of immovable property;
6. Deliver a copy of the location and other matters registered in relation to land possession to legally authorized person;
7. Register divided or merged possession of land based on cadastre plan information; issue certificate of such registration;
8. Register cancelled title deed, court injunction, mortgage of banks and other lawful bodies;
9. Register immovable property belonging to the City Government; issue title deed of same;
10. Correct records of immovable property, where it is incomplete or inaccurate, according to relevant provisions of the Civil Code;
11. Perform other legal functions designated to it by the Agency.

## Part Two

## Appointment, Power and Function of the Director and Deputy Directors of the Agency

### 9. Director of the Agency

1. The director shall be appointed by the Mayor up on recommendation by the City Manager.
2. Term of office of the director shall be three years.
3. Notwithstanding the provisions of sub-article 2 of this Article, the director may be reappointed for a second term.

### 10. Power and Function of the Director

The director shall:-

1. supervise and administer the Agency; execute the powers and functions of the Agency;
2. without prejudice to the provisions of sub-article /1/ of this Article, the director shall discharge the following power and functions;-

ሀ. የክፍለ ከተማ ኤጀንሲ ጽህፈት ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት ይከታተላል፣ ይገመግማል፣

ለ. ለኤጀንሲው የስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለበታች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፣

ሐ. ከኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባር ጋር አግባብነት ያላቸውን ሀገር አቀፍ መርሆዎች፣ ደረጃዎችና የአሰራር ስነ ስርዓቶች መከበራቸውን ያረጋግጣል፣

መ. በአስተዳደሩ የተመዘገበ የመሬት መረጃ ዓይነት ያሻሽላል፣

ሠ. ህጋዊ የማይንቀሳቀስ ንብረት ልዉውጥ እንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዙ የምዝገባ ሂደቶችን የሚመለከት የአስተዳዳሩን እስታስቲክስ መረጃ ያዘጋጃል፣ አመራር ይሰጣል ፣

ረ. በሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት ሠራተኞችን ይመለምላል፣ ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

ሰ. የተቋሙ ስራዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ መከናወናቸውንና የተዘጋጁ መሳሪያዎች በተሟላ ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

ሸ. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፣

በ. የኤጀንሲውን የመካከለኛና ረጅም ጊዜ እቅዶችን ለከተማው ስራ አስኪያጅ በማቅረብ ያስፀድቃል፣ ሲፀድቅም ይተገብራል፣

ተ. የኤጀንሲውን የስራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለከተማው ስራ አስኪያጅ በየሶስት ወራት ያቀርባል::

## ፲፩. የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተሮች አሿሿም

፩ የኤጀንሲው ምክትል ዳይሬክተሮች በከተማዉ ስራ አስኪያጅ አቅራቢነት በከንቲባው ይሾማሉ::

፪ የምክትል ዳይሬክተሮች የስራ ዘመን የዳይሬክተሩ የስራ ዘመን ይሆናል::

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገዉ ቢኖርም ምክትል ዳይሬክተሮች ለሁለተኛ ጊዜ ሊሾሙ ይችላሉ::



a) Follow up and evaluate the function and responsibilities of offices of the Agency at Sub-city;

b) Partially delegate, to the extent necessary for expediency of works of the Agency, his power and function to the subordinate;

c) Ensure the observance of national standards, principles and procedures relevant to the power and functions of the Agency;

d) Improve data recorded by the City Government;

e) Prepare statistical information of the City Government concerning process of registration related to legal exchange of immovable property; give direction regarding same;

f) Recruit, employ and dismiss employee in accordance with civil service law;

g) Ensure that functions of the Agency are effectively carried out and the existing instruments are fully utilized;

h) Represent the Agency in its relationships with third parties;

i) Submit to the City Manager and implement up on approval the medium and long term plans of the Agency;

j) Prepare and submit to the City manager quarterly performance and accounting reports of the Agency.

## 11. Appointment of the Deputy Directors

1. The deputy directors of the Agency shall be appointed by the Mayor up on recommendation of the City Manager.
2. The term of office of the deputy directors shall be that of the Director.
3. Notwithstanding the provisions of sub-article 2 of this Article, the deputy directors may be reappointed for a second term.

**፲፪. የምክትል ዳይሬክተሮች ስልጣንና ተግባር**

፩ የኤጀንሲው ዳይሬክተር በሌለበት ወቅት በእሱ ተለይቶ የተወከለው ምክትል ዳይሬክተር እንደ ሁኔታው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ወይም ፫ ከተገለፀው ተግባር በተጨማሪ እሱን ተክቶ ይሰራል፣

፪ የኤጀንሲው ምክትል የቅየሳ ዳይሬክተር የማይንቀሳቀስ ንብረት ቅየሳን የተመለከቱ ተግባራትን ያከናውናል፣

፫ የኤጀንሲዉ ምዝገባና መረጃ ምክትል ዳይሬክተር የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባንና መረጃን የሚመለከቱ ተግባራትን ያከናውናል፣

፬ እያንዳንዱ ምክትል ዳይሬክተር የኤጀንሲውን ግብና ዓላማ ለማሳካት በዳይሬክተሩ ወይም በቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ይፈጽማል፣

**12 . Power and Function of the Deputy Directors**

1. The deputy director specifically delegated shall, in addition to functions provided under sub-article 2 or 3 of this Article, as the case may be, represent the Director in his absence;
2. The survey deputy director shall carry out functions relating to survey of immovable property;
3. The registration and information deputy director shall carry out functions relating to registration and information of immovable property;
4. Each deputy director shall carry out other functions designated by the Director or the Board with the view to achieve the goals and objectives of the Agency.

**፲፫. የጽህፈት ቤት የሥራ ኃላፊዎች አሿሿም**

፩ እያንዳንዱ የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ዳይሬክተር በስራ አስኪያጁ አቅራቢነት በከንቲባው ይሾማል::

፪ እያንዳንዱ የክፍለ ከተማ ጽህፈት ቤት ምክትል ዳይሬክተር በኤጀንሲዉ ዳይሬክተር አቅራቢነት በስራ አስኪያጅ ይሾማል::

**13. Appointment of Officials of the Office**

1. The director of each office shall be appointed by the Mayor up on the recommendation of the City Manager.
2. Each deputy director of sub-city Office shall be appointed by the City Manager up on recommendation of Director of the Agency.

**፲፬. ከኃላፊነት ስለመታገድ**

፩ የኤጀንሲው ወይም የጽህፈት ቤት ዳይሬክተር ወይም ምክትል ዳይሬክተር የማይገባ ተግባር ፈጽሞ ሲገኝ ስራ አስኪያጁ ከኃላፊነት ሊያግደው ይችላል::

፪ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ከኃላፊነት የታገደ ዳይሬክተር ወይም ምክትል ዳይሬክተር ለከተማው አስተዳደር ከታገደበት ቀን ጀምሮ ባሉ አምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል::

፫ የከተማው አስተዳዳር በዳይሬክተሩ ወይም ምክትል ዳይሬክተሩ ላይ የቀረበውን ክስ ፍሬ ነገር የሚመረምር አንድ የዲሲኘሊን ኮሚቴ ይሰይማል፣

፬ ኮሚቴው ማስረጃውን እና ፍሬ ነገሩን ካየ በኋላ ከአስተያየት ጋር ለአስተዳዳሩ ለውሣኔ ያቀርባል::

**14. Suspension from Responsibility**

1. The City Manager may suspend from responsibility the director or deputy director of the Agency or an Office where he is found committing improper act.
2. The director or deputy director suspended from his responsibility according to sub-article (1) of this Article may present his grievance to the City Government within five working days from the date of such suspension.
3. The City Government shall designate a committee to examine facts of the allegation up on the director or deputy director suspended.
4. Having examined the facts and evidence, the committee shall submit its findings to the City Government along with its recommendation .

## ክፍል ሶስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፭. የበጀት ምንጭ**

የኤጀንሲው የበጀት ምንጭ:-

፩ ከአገልግሎት ከሚሰበስበው ክፍያ፣

፪ ከከተማው አስተዳደር ከሚመደብ የድጎማ በጀት፣ እና

፫ ከሌላ ከማንኛውም ህጋዊ ምንጭ ይሆናል::

**፲፮. የሂሣብ መዛግብት**

፩ ኤጀንሲው ትክክለኛና የተሟሉ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል፣

፪ ዳይሬክተሩ የኤጀንሲውን ዓመታዊ ሂሳብ፣ ሀብትና እዳ፣ ወጪና ገቢ ከነማብራሪያው ይይዛል፣

፫ ስራ አስኪያጁ የኤጀንሲውን አመታዊ ሂሣብ ለማስመ ርመር የውጭ ኦዲተሮችን ሊሰይም ይችላል::

**፲፯. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዳ ደንብ ሊያወጣ ይችላል::

**፲፰. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተካተቱት ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም::

**፲፱. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ**

**ግንቦት ፴ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.**

**ኩማ ደመቅሳ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## Part Three
## Miscellaneous Provisions

**15. Source of Budget**

The source of budget for the Agency shall be from:-

1. the service fee it collects,
2. the budget allocated to it by the City Government, and
3. any other legal source.

**16. Books of Account**

1. The Agency shall keep accurate and complete books of account;
2. The Director shall keep the yearly account, asset and liability, income and expenditure along with its statement;
3. The City Manager may appoint external auditors to examine yearly accounts of the Agency.

**17. Power to Issue Regulation**

The Addis Ababa City Government Cabinet may issue regulation to implement this proclamation.

**18. Inapplicable Laws**

Any proclamation, regulation, and practice inconsistent with this proclamation shall not be applicable with regard to matters stated in this proclamation.

**19. Effective Date**

This proclamation shall enter into force as of 7th day of June/2010.

**Done at Addis Ababa this 7th day of June 2010**

**Kuma Demeksa**

**Mayor of Addis Ababa City**